Career READINESS

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)

2018–2019

# አዲስ! ለሥራ ፕሮግራሞች የመመዝገቢያ አማራጮች



## ማንኛውንም ሥራ የምትመረጥ(ርጪ) ቢሆን የትኛው ይሆን?

አሁን መወሰን አይኖርብህም/አይኖርብሽም፣ ነገር ግን ብታዩዋቸው ሃሳብ (ምርጫ) ለመስጠት የሚችሉ አዳዲስ ፕሮግራሞች አሉን። ኮሌጅ ብትከታተል(ይ)ም ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ በስራ ላይ ብትሰማራ(ሪ)ም ፣ የኢንዱስትሪ ሰርተፊኬት፣ እና የተጨባጩ-ዓለም ልምድ ጥሩ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችልህ(ሽ) የኮሌጅ ክሬዲት ለማግኘት ትችላለህ/ትችያለሽ።

### አዳዲሶቹ ፕሮግራሞች ምን ምን ናቸው?

ፕሮግራሞቹ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እና የበረራ ኢንጅነሪንግ፣ ፋይናንስ፣ እና ማስተማር ድረስ ይደርሳሉ/ይለያያሉ። ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በምትመረቅ(ቂ)በት ጊዜ በአንዳንዶቹ ፕሮግራሞች ያለ ምንም ክፍያ ወይም በቅናሽ ክፍያ የሁለት ዓመት አሶስየትስ ዲግሪ ልታገኝ(ኚ)በት ትችላለህ/ትችያለሽ። በኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት Edison High School of Technology አዳዲስ ፕሮግራሞችን ጨምሯል። በሚቀጥለው ዓመት በአዲሱ state-of-the-art የሥራ ማቀላጠፊያ ማዕከል/ፋሲሊቲ ይገኛል። በስተጀርባው ካለው ቻርት ላይ ሁሉንም ዝርዝር ለማግኘት ይቻላል።

### አዳዲሶቹ ፕሮግራሞች በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይሰጣል?

ለ 2018–2019 የትምህርት ዓመት እነዚህ አዳዲሶቹ ፕሮግራሞች የሚገኙት በተወሰኑ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው። ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሥራ የሚያዘጋጁ መንገዶች አሏቸው እና የአንተ(ቺ) ካውንስለር የበለጠ መረጃ ሊሰጥህ(ሽ) ይችላል። www.montgomeryschoolsmd.org/career-readiness/plans/hs-plans.aspx

### እኔ ከምፈልጋቸው አዳዲስ ፕሮግራሞች አንዱ ወደሚሰጥበት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መቀየር እችላለሁ?

ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከምድብ /ክለስተር ት/ቤቶች ተማሪዎች የሚፈልጉት የሥራ ፕሮግራም ሙያ ትምህርት ወደሚሰጥበት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሊዛወሩ ይችላሉ። እንደፕሮግራሙ ሁኔታ እና ጥቂት መቀመጫዎች ብቻ ስለሚኖሩ የምድብ/ክለስተሮች ተሳትፎ ይለያያል። የተለያዩ ዝርዝሮችን ለማግኘት/ለማወቅ በስተጀርባው ተመልከት(ቺ)።

### የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል?

አዎን። በአዲሱ ፕሮግራም ከገባህ(ሽ) ከተወሰኑ የመቆሚያ ስፍራዎች ፕሮግራሙ እስከሚሰጥበት ት/ቤት ድረስ(በሞንጎመሪ ኮሌጅ ካምፓስ የሚሰጥ ፕሮግራም ካልሆነ በስተቀር) MCPS የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

### ከአካባቢዬ ምድብ ት/ቤት ውጪ ትምህርት የምማር ከሆነ፣ በተጠየቀው ትምህርት ቤት ሙሉ ጊዜ እከታተል ይሆን?

እንደፕሮግራሙ ሁኔታ ይወሰናል። በክላርክስበርግ፣ በማግሩደር፣ እና በዋትኪንስ ሚል አዳዲሶቹ ፕሮግራሞች የሚጀምሩት ከ9ኛ ክፍል ሲሆን ሙሉ-ጊዜ ነው። ሌሎች ፕሮግራሞች እንደ እሳት አደጋ የመከላከል ሳይንስ * የሚጀምሩት በ 11ኛ ክፍል ስለሆነ በምትማር(ሪ)በት የአካባቢ ት/ቤት እና በጌተስበርግ የህብረተሰብ ደህንነት ስልጠና አካደሚ መካከል ያለህ(ሽ)ን ጊዜ ለማከፋፈል ትችላለህ/ትችያለሽ።

### ለ 2018–2019 መቼ ነው ማመልከት ያለብኝ?

የማመልከቻ ቅጾች እና የጊዜ ሠሌዳዎች ጃኑዋሪ መግቢያ 2018 በ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice/ይለጠፋል/ፖስት ይደረጋል።

ኤዲሰን በአዳዲሶቹ ፕሮግራሞች ወይም በቀድሞዎቹ ፕሮግራሞች ፍላጎት ካለህ(ሽ) የማስገቢያ ሂደቱን ከዚህ ለመከታተል ትችላለህ/ትችያለሽ:- www.montgomeryschoolsmd.org/schools/edison/about/enroll.aspx





### ተጨማሪ ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማንን ማነጋገር አለብኝ?

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ:-www.montgomeryschoolsmd.org/career-readiness/ ወይም ፕሮግራሙ በሚሰጥበት ት/ቤት ሱፐርቫይዘር ያግኙ።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ROCKVILLE, MARYLAND

*ይህ ፕሮግራም ከ 2019 የበጀት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ባጀት ማጽደቅ ጋር የተያያዘ ነው።

| ትኩረት | ቦታ | ለማግኘት | ምዝገባ | ብቃት** | አመልክት(ቺ) |
|---|---|---|---|---|---|
| **በ ቴክኖሎጂ፣ በኔትዎርክ፣ እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አዲስ ስልት/መንገዶች።** | | | | | ፍላጎት ካለህ(ሽ) በ አማካይነት ማመልከቻህ(ሽ)ን አቅርብ(ቢ) Division of Consortia Choice and Application Program Services<br><br>አስፈላጊ ከሆነ፣ የተማሪዎች ምርጫ/ምልመላ የሚደረገው በእጣ ይሆናል።<br><br>ቅጾች እና የጊዜ ሠሌዳዎች ጃኑዋሪ መግቢያ 2018 በድረ-ገጽ ይለጠፋሉ/ፖስት ይደረጋሉ። www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice/ |
| የኔትዎርክ ኦፐሬሽን እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | ክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት/ Clarksburg High School | የኢንዱስትሪ ሠርተፊኬት፣ ኮሌጅ ክሬዲት፣ አሶስየት ዲግሪ በአፕላይድ ሳይንስ ከሞንጎመሪ ኮሌጅ (Industry certification, college credit, associate's degree in applied science from Montgomery College) | 9ኛ ክፍል የሚጀምሩ የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች | ለ ክላርክስበርግ፣ ደማስከስ፣ ሰኔካቫሊ፣ እና ዋትኪንስ ሚል ምድብ/ክለስተሮች ተማሪዎች የተወሰነ ነው። (10 መቀመጫዎች ይኖራሉ) | |
| **የበረራ ትምህርት/ጥበብ እና የበረራ ምህዋር** | | | | | |
| በረራ እና የአውሮፕላን ሥርአቶች/systems | ማግሩደር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | አውሮፕላን አብራሪነት የግል ፈቃድ/ላይሰንስ፣ በርቀት ፓይለት/አብራሪ ሠርተፊኬት፣ የኮሌጅ ክሬዲት | 9ኛ ክፍል የሚጀምሩ የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች | ለጌትስበርግ፣ ማግሩደር፣ ሮክቪል፣ እና ሼርውድ ምድብ ተማሪዎች የተወሰነ (32 መቀመጫዎች ይኖራሉ) | |
| **ከሙያ/ሥራ ጋር የሚገናኝ ፕሮግራም ዓለምአቀፍ ባካሎሬት/ International Baccalaureate (IB)** | | | | | |
| የላቀ/ከፍተኛ ምህንድስና፣ ኮምፒውተር ሳይንስ፣ የህፃናት አስተዳደግ፣ ፋይናንስ፣ የጤና ሙያ እና የሥነ ህይወት ሳይንስ/ባዮሳይንስ፣ እና የመስተንግዶ ማኔጅመንት | ዋትኪንሚልስ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Watkins Mill High School) | IB ዲፕሎማ፣ ኮሌጅ ክሬዲት | 9ኛ ክፍል የሚጀምሩ የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች | ለ ክላርክስበርግ፣ ዳማስከስ፣ ጌትስበርግ፣ ሴኔካ ቫሊ፣ እና ዋትኪንስ ሚል ምድብ ተማሪዎች የተወሰነ (32 መቀመጫዎች ይኖራሉ) | |
| **ስለ እሳት ሳይንስ እና መታደግ/ማትረፍ*** | | | | | |
| የእሳት አደጋ መከላከልና ቁጥጥር እና አስቸኳይ የህክምና ቴክኖሎጂ | የአካባቢ/ የቤት ት/ቤት እና የካውንቲው የህዝብ ደህንነት ስልጠና አካደሚ | የኢንዱስትሪ ሠርተፊኬት፣ የኮሌጅ ክሬዲት | 11ኛ ክፍል ይጀመራል | ለ ክላርክስበርግ፣ ደማስከስ፣ ጌትስበርግ፣ ማግሩደር፣ ሴኔካ ቫሊይ፣ እና ዋትኪንስ ሚል ምድብ/ክላስተሮች ተማሪዎች የተወሰነ (32 መቀመጫዎች ይኖራሉ) | |
| **ቀደምት ኮሌጅ፣ ለረዳት የስነጥበብ መምህርነት** | | | | | |
| የሁለተኛ ደረጃ ሂሳብ | ሞንጎመሪ ኮሌጅ፣ ሮክቪል ካምፓስ/Montgomery College, Rockville Campus | ረዳት የስነጥበብ ዲግሪ በሁለተኛ ደረጃ ሂሳብ | የሚጀምረው ከ11ኛ ክፍል ነው። | ከሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (20 መቀመጫዎች ይኖራሉ) | |
| **ህግ አሰፈጻሚነት እና መሪነት** | | | | | የ ኤዲሰንን የምዝገባ ሂደትበ www.montgomeryschoolsmd.org/schools/edison/about/enroll.aspx ይከታተሉ |
| ህግ አስከባሪነት፣ የወንጀል ዳኝነት | ቶማስ ኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የአካባቢ/ የቤት ውስጥ ት/ቤት | የኮሌጅ ክሬዲት፣ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስልጠና በ MoCo የፖሊስ መምሪያ እና በሜሪላንድ ስቴት ፖሊስ የሚሰጥና በወንጀል ዳኝነት ወደ አሶስዬት ዲግሪ የሚያመራ | ከ11ኛ ክፍል ይጀምራል። | ከሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚመጡ ተማሪዎች | |
| **ስለ ኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች ደህንነት/Cybersecurity Capstone** | | | | | |
| የግንኙነት አውታሮችን እና መረጃዎችን ለመጠበቅ/ለመከላከል የኮምፒውተር ሲስተም እና ቴክኖሎጂዎች | ቶማስ ኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የአካባቢ/ የቤት ውስጥ ት/ቤት (Thomas Edison High School and home school) | የኢንዱስትሪ ሠርተፊኬት፣ እና የኮሌጅ ክሬዲት | ከ11ኛ ክፍል ይጀመራል | ከሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች | |
| **የጤና ሙያዎች አካደሚ (ቀጣይ)** | | | | | |
| መድኃኒት እና የጤና ሳይንስ | ቶማስ ኤድሰን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የአካባቢ/ የቤት ውስጥ ት/ቤት | የኢንዱስትሪ ሠርተፊኬት፣ ኮሌጅ ክሬዲት | ከ10ኛ ክፍል ይጀመራል | ተማሪዎች ከሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች | |

*ይህ ፕሮግራም ከበጀት ዓመት 2019 የሥራ ማስኬጃ በጀት መፅደቅ ጋር የተያያዘ ነው።

** ቦታ ከተገኘ እና የመጓጓዣ አገልግሎት የሚገኝ ከሆነ ተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምድቦች/ክለስተሮች ይኖሩ ይሆናል።